# <u>እቴሜቴ</u>

እቴሜቴ ፤ ያገር በሽታ
ኦነግ መጥቶ ፤ ምን አለሽ ማታ
    ምንም ምንም ፤ ምንም አላለኝ
    አገር እንበትን ፤ እናፍርስ አለኝ
አታፈርሺም ፤ ማን ይለቅሻል
የህልም እንጀራ ፤ ከንቱ ያምርሻል
    ማላ ማላ ፤ የጎበዝ ማላ
    ሲያምርሽ ይቅር ፤ ያንቺ ግንጠላ ።

---

ካገሬ በላይ ፤ ኦነግ ሰፍሮ . . .  ኦነግ ሰፍሮ
ልገንጥል ብሎ ፤ ሄዶ በሮ . . .  ሄዶ በሮ
    እኔን ያብረኝ ፤ ያክንፈኝ . . . ያክንፈኝ
    መገንጠል እንደሁ ፤ አይገኝ . . . አይገኝ
ኦነግ ተፈጥሮው ፤ አድር ባይ ነው . . . አድር ባይ ነው
ግንቦቴ አቋሙ ፤ ወላዋይ ነው . . . ወላዋይ ነው
    ተማክሮ መጥቶ ፤ ሲመለስ . . . ሲመለስ
    በየፓልቶኩ ፤ ሲለቀስ . . . ሲለቀስ
ሻቢያ ቆሞ ፤ ሲያስቀድስ . . . ሲያስቀድስ
ኦነግ ፈንድቆ ፤ ሲደንስ . . . ሲደንስ ።

---

    ሊገነጥል . . . ባገር መክሮ
    ተደብቆ . . . ተሰውሮ
    አለማወቅ . . . ወይ ደንቆሮ
    አለማወቅ . . . ወይ ደንቆሮ ።

ታዛቢው . . . 09/15/2011